# የቡቱቱ እናት ሲታሰቡ

## ከአይኔ በላይ?

### ክፍል ሁለት

ሳያዩ ያመኑ ብጹአን ናቸው ቢባልም ለዘንድሮው ለተተበተበው ታሪካችን እማኝ ለመሆን ከአይኔ በላይ የማምነው አይኖርምና ያየሁትን ለመግለፅ ነው የምሞክረው::

ሃሳቤና ገለጻው የመነጨበትን በጉልህ ለማሳየት በእድሜዬ ውስጥ ሰማእትነትን በቀዳር አንድ የማስቀምጣቸው ወላጆችን ነውና ለዛሬው ከአይኔ በላይ ጽሁፌ ያጨኳቸው እናት የቡቱቱ እናትን ታሪክ ይሆናል፡፡

ዛሬ ቁልልና ክምር የውሸት የገለባ ተራራ የተከመረበት የኢሕአፓን የሰማኢታት ገድል ያየሁትን በአጭሩ ስዘክር ለዛሬ በወያኔ እየተበላች በባእድ እየተፋቀች ላለችው ኢትዮጰጵያ አይጠቅምም የሚል አታካሮ የሚያነሱ ታሪካችንን ለሚያድበሰብሱ ዕሁፉ የኔ ነውና እይታውም የአይኔ ነውና በእምነቴ ኣትምጡ ነው የምለው::

የቡቱቱ እናት ታሪክ ከተድበሰበሰ የወያኔ ሰንደቅ አላማ ጨርቅ ነው አባባል እውን ይሆናልና!

ባለፈው ክፍል አንድ ለይ የዘከርኩት የብላቴናው ውልጃቦ ታሪክ ለአንባቢ ከንፈር ላያስመጥጥ ቢችል እንኳ ለእኔ በአይኔ ያየሁት ነውና ለዛሬ ጉዞዬ ነዳጅ የሚሆነኝ አቀጣጣይ እውነታ ስለሆነ የዛሬው የቡቱቱ እናት ታሪ ክ ቢብስ እንጂ አያንስብኝም፡.....

ቁልቁል በሚወርደው የመንደራችን ኮረኮንች መንገድ ጨርሰው ወደ ግራ ሲታጠፉ ላፍታ ቆም ብለው ዞር በማለት የተሰበሰብነውን ወጣቶች በሀዘንና በፍቅር ከሚመለከቱን የቡቱቱ እናት አንዷ ነበሩ፡፡ ነፍስ ካወቅኩኝ ጀምሮ በደንብ የማውቀውና ዋስይሁን ከሚለው መጠሪያ ስሙ ይልቅ ቡቱቱ የሚባል ቅፅል መጠሪያው የሚዘወተርለት ልጅ ለምን ቡቱቱ ተባለ ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከኛ የባሰ የ መጨረሻው የደሃ ልጅነቱ መልበስ እንኳን ስላላሰቸለው እላዩ ላይ የነተበ ልብሱ ነበር ዋስዬን ቡቱቱ ያስባለው ሌላ አይደለም::

እናትየው በምን ግዜ ወይም በምን ዘመን እዛ ሰፈር እንደገቡ ባላውቅም እህት ወንድም አጎት አባት ምንአለፋችሁ ዘመድ አዝማድ ባል ጭምር የላቸውም::ዋስይሁንን አንቺ ብለው በሴት ለምን እንደሚጠሩ አላውቅም::የማውቀው በየሰዉ ቤት በእሳት መንደድ በጪስ መጨስ የቡቱቱ እናት ላይ ስርአቱ የፈረደባቸው ፍርደኛ አርጎአቸዋል፡፡

እናት በክፍያ መልክ የሚሰጣቸውን እንጀራ በተገኘው በልቶ አዳሪው ቡቱቱ ከስምንተኛ ክፍል ትምርቱን ያቋረጠው 1967 አ.ም መጀመርያው ላይ ነበር:: ያቆመው እግዬ ከዛሬ ጀ ምሮ ጋጋሪነትሽ እዚህ ላይ አቆመ  የሚል ለማብሰር ሲል ቴሌኮሙኒኬሽን በቁፋሮ በመቀጠሩ ነበር:: ለእናቱ ሲል በቁፋሮ የጀመረው ትጉህ ስራተኛ ስላሰኘው ዘመድ አልባው ቡቱቱ በአመቱ በኬብል ዘርጊነት ወደ 75ብር ደሞዝኝተነት ተሸጋገረ::

የቡቱቱ እናት ጪስ ያጨሰው አይናቸው ገለጥ ወደማለትም መሸጋገሩን በአይኔ ተመልክቻለሁ:: የቡቱቱን እናት በ1969 አም ላይ ሳያቸው ያ ገለጥ ያለው አይናቸው የባሰውን ሞጭሞጭ ከእድሜያቸው ከ 10 -20 ጨምረው ጎብጠው ብቻቸውን እያጉረመረሙ አንዲት ትንሽ የምሳ ሳሃን በአረንጓዴ ዳንቴል ሸፍነው፤ ቡቱቱ በመጀሪያ ደሞዙ በህይወታቸው የመጀመሪያ የሆነውን የገዛላቸው ሽራ ጫማ ብትንትኑ ወጥቶ እሱን እየጎተቱ ሰሄዱ ነበር 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ያየሁቸው::

በ1969 አ.ም ውሰጥ ያ ተውሳክ መንግስት የገደላቸውንም ያልገደላቸውንም ከተለያዩ መስርያ ቤቶች ይሰሩ የነበሩ ባለሙያዎች 700 ያህሉን በየቦታው የለጠፈውን የ ይፈለጋሉ ፖስተር ታስታውሳላቸሁ?አዎ እዚያ ላይ ከገደለው በሁላ የጠፋ ብሎ ስሙን የለጠፈውአንዱ የጋጋሪዋ ልጅ ምስኪኑ ዋስይሁን ቡቱቱ ነበር::በእርግጥ እናቱ በእሳት እየተጠበሱ ያሳደጉት ዋሲሁን ተረሽኗል !! እናትየው ግን በቁማቸው ቀልጠው አለቁ ! በጥዋት ያቺን መከረኛ ግማሽ ቂጣ የምትይዝ ሰሃን ቋጥረው ከ5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ይጀምሩና ከርቸሌ ያጉዙና መጨረሻቸው ከጎበዙ 6ኝንና 3ኛን አዳርሰው ምንም መልስ ሴያጡ ወደ ደሳሳ ጎጆአቸው ሂደው ድፍት ይላሉ:: በየቀበሌው በየከፍተኛው በመዞር ለዋስይሁን ስጡልኝ የመጀመሪያው ጥያቄአቸው ይሆናል::

መልሱ ጠርተን ጠርተን አጣነው ተብሎ ያቺ ሰሃን ለአሮጊቷ ትመለሳለች::እባክህ ልጄ ቡቱቱዬ ብለህ እንደገና ሞክር ይላሉ/ደህና ፖሊስ ወይ አብዮት ጥበቃ ወይ ምግብ አመላላሽ ተረኛ እስረኛ ከገጠ ማቸዉ ይሞክርላቸዋል:: መልሱ የለም ነው:: እኝህ እናት እስከ 1971አ.ም ድረስ የአዲስ አበባን ወህኒ ቤት/ማዕከላዊ/ጣቢያዎች/ከፍተኛች/ቀበሌዎችን/ አሰሱ/አሰሱ ግን ቡቱቱ አተልገኘም::በተለይ ታስረን ከተፈታን በኋላ ሰፈር አካባቢ ሰብሰብ ብለን ከቆምን ለአይን ድንግዝግዝ ሲል ይመጡና እጃቸውን ወደኋላ አጣምረው ድክም ባለና እንባ በሸረሸረው አይናቸው አንድ በአንድ ይመለከቱንና ኡፍፍፍ!! ብለው የመተንፈስና የድካም ድምፅ በሃዘን ደባልቀው ካሰሙን በኌላ ወደ ቁልቁል ጎተት ብለው ሲሄዱ እስካሁን ወለል ብለው በቁጭት ይታወሱኛል::

ለመኖር የመጋገር አቅማቸው በአንድዬ ልጃቸው ሀዘን ተሰብሮ በጥዋት ይነሱና ወደበርበሬ በረንዳ ሂደው በትንሽ ሳንቲም ለሃብታም ሲቀነጥሱ ውለው በአገኟት ሳንቲም ላምባና/ናፍጣ አንድ ዳቦ ከሲሎን ሻይ ቤት ይገዙና ከሻይ ቤቱ በራፍ ላይ አንድ የቆየ

የተጣመመ ኤሌክትሪክ ምሰሶ ይደገፉና ፊታቸውን ወደ ቴሌኮምኒኬሽን ያዞሩና እንደ ደጀ ሰላም ተሳልመው የሆነ ነገር አማትበው በተለምዶ አካሄዳቸው ቁልቁለቱን ተያይዛው ጭልጥ ይሉ ነበር::

ስለሳቸው ላጠቃልል::

እኔና በቅርብ የምንተዋወቅ ጓደኛዬ አንድ አመሻሽ ላይ የቡቱቱ እናት ወደ ቴሌ ዞረው የሚያማትቡት ምንድነው ? በማለት ከጀርባቸው ቀስ ብለን ኮቴ አጥፍተን ስናዳምጥ እንዲህ ይ ሉ ነበር:: በጣም ቀስ ባለ ድምፅ .....

ቡቱተ/ ቡቱቱዬ/ ዋሴ /ዋስዬ/ደህና ዋልሽ ደህና አመሸሽ?ለኔ አታስቢልኝ:: ላምባ ገዝቻለሁ ፉርኖም አግኝቻለሁ አይዞሽ መሬቱ ይመችሽ ዋስዬ ደህና እደሪልኝ:: ነገ ደግሞ መጥቼ ሰላም እልሻለሁ ዋቀዮ ይጠብቅሽ ደህና እደሪልኝ ይሉና /ያቺ እንባዋ ያለቀውን አይናቸውን ጭምቅ አድርገው የቀራትን ትንሽ ዘለላ እንባ ያንጠባጥቡና ቀስ ብለው ፊታቸውን አዙረው ቁልቁለቱን መሰስ ይላሉ ወደዚያ በመቃብር በሚመስል ቤታቸው::

አንባቢ የቡቱቱ እናት ስቃይ ያቆመው ስደት ከመጣሁ በኋላ በወሬ በወሬ ሳፈላልግ በሞቱ በስንተኛው ቀን እንኳ እንደሆነ አይታወቅም እቤታቸው ደርቀው ተገኙ የሚል በወሬ ከቤተሰቦች አገኘሁ::

አንድ ቀን እንኳ የላምባ መግዣ ሳልረዳቸው ይፅፅተኛል:: የእንደ ዋስይሁን እናት አይነቶች በመቶ ሺ ይቆጠራሉ:: የአባቶችም ታሪክ እንዲሁ:: ያ የወላጅ እናቱን ህይወት የ ህገሩንም ገፅታ ለመለወጥ ወጥቶ የቀረው ቡቱቱና በቡቱተ ሀዘን እንደሻማ የቀለጡ እናት በኢህአፓ የታሪክ ቅርስ ውስጥ ድርሻ እዳላቸው በቅጡ ልንረዳው ይገባል::

የቡቱቱንና የእናቱን ቤት ያዘጋው ታሪክ ፍፃሜው አልተገባደደምና ታሪካቸውን ኢሕአፓን ማለት ነው እንደ አይን ብሌን አይንፈስብሽ አይብነንብሽ ብለን ልንከባከብ ይገባናል::

በአይኔ ያየሁትን እየጨመቅኩኝ የማንጠፉጥፈው ስሜቴን ላጋራችሁ ነው:: በኢህአፓ ላይ ቡቱቱ መፍጠር በቡቱቱ እናት ሰማእትነት ላይ ማላገጥ አልያም የዚያን ታሪክ ያልተጋሩ ተብሎ የማይሰማቸው አፍቅሮተ ራስ ያስብላል::

ለጋው ዋሲሁን ቡቱቱ በለጋነቱ የተቀጨበትን እኛ ጋጋሪ እናት የቀለጡበትን ታሪክ መጠበቅ አለብን ስል ለመጪው ትውልድ በታሪክነት ለማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ያላገባደድነውን ትግላችንን እንድንገፋ በአንድነት ያቆላልፈናል ከሚል ፅኑ ኅዳዊ እምነት በመነሳት ነው::

እነ ዋሴ ቡቱቱና እናቱ በደማቸውና በመከራቸው የገነቡትን የእውነት ሃውልት ውስጣችን በበቀለ የበቀል ፅንስ ተሳክረን በቤታችን የምንፈታውን የቤታችን ችግር አደባባይ አስጥተን የነቡቱቱንና የእናቱን በድን ባንጎረብጥ የተሻለ ይመስለኛል::

ኢሕአፓ በሚያደርገው የውስጥ ጉባኤ ይሁን የውስጥ ስራ ዙሪያውን በመቶ ሺህ ሰማእታት የቡቱቱን እናት ጭምር እንዳጀበው አለማወቅ ራስን በራስ ራስ እከሌ የሚል

መአረግ ያሰጥና ራስን ማዞር ያስከትልና የራስ ቤት ላይ እሳት ያስለኩስና የራስ ታሪክን ማቃጠል ይመጣል፡፡ እንደ ዋሲሁን እናት ብዙ ሺህ ወላጆች ተንከራተው አልፈዋል ፡፡ብዙሺህዎች አሁን እህህ ይላሉ ኢህአፓ የነዚህን እልፎች የተሰዉበትን አርማ አንስቶ እስከ ህልፈተ አለም ትግሉን ይቁጥላል፡፡

የኢህአፓነት ሀ ሁ ውሳኔዎች በስምምነት ገፋ ሴልም ባብላጫ ድምፅ መሆኑን አለማወቅ ፈር መሳትን ያስከትላል፡፡አልጋ በአልጋ ያልሆነው የ36 ዓመት ትግል ከሁሉ በፊት የራስን ስሜት መግራትን ግድ ይላል፡፡ ዲሞክራሲያን በሃገር ለማስፈን የሚታገል ደግሞ ራስን በመጀመሪያ ለብዙሃንያስገዛል እንጂ የተሸነፈን ሃሳብ ያመነጨው አናሳ ክፍል በቤት ላይ ቤት ሰርቶ የኢህፓን ስም ይዞ ጎጆ አይወጣም፡፡ እድሜ ለነ ቡቱቱ እናት ጧፍ ሁነው እየመሩን ነውና ትግሉን እንቀጥላለን! ኢሕአፓነት የሚያወርዱት የሚሰቅሉት የግድግዳ ጌጥ ሳይሆን በህገ ደምብ የሚከበር የደም ህውልት እንጅ!

ልብ ላጣ ልብ ይስጥ…………………
ይቀጥላል

ዮሃንስ ታከለ